www.ethiopianlawgroup.com

ማለት መደበኛ ወይም ወታደራዊ ፍርድ ቤት ነው፤4/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ወይም የሕግ ሰውነት ያለው ሰው ነው፤

5/ በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል።

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተመለከቱ የወንጀል ድርጊቶችን ፈጽሟል ተብሎ ተጠርጥሮ በሚፈለግ፣ በምርመራ ላይ ያለ፣ የወንጀል ክስ የተመሰረተበት ወይም የጥፋተኝነት ፍርድ ውሳኔ የተላለፈበት ሰው ወይም የሽብርተኛ ድርጅት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

4. <u>ዓላማ</u>

ይህ አዋጅ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

1/ በተለያዩ የወንጀል ድርጊቶች የተሳተፉ ሰዎች ለድርጊታቸው የወንጀል ተጠያቂነታቸውን በጠቅላላው በመሰረዝ ወደ ሕብረተሰቡ ተቀላቅለው በሀገር ግንባታ ውስጥ የበኩላቸውን ድረሻ እንዲያበረክቱ ማድረግ፤

2/ የፖለቲካ መብታቸውን ተግባራዊ ለማድረግ በመንቀሳቀሳቸው ምክንያት የወንጀል ተጠያቂነት ሊያስከትል ይችላል በሚል ስጋት በተለያዩ የዓለም ሀገራት የሚገኙ ኢትዮጲያዊያንና ትውልደ ኢትዮጲያዊያን ምህረት በመስጠት ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤

3/ ጥላቻና የእርስ በእርስ ጥርጣሬን በማስወገድ በመፈቃቀድና በአንድነት የተጀመረውን የሀገራችን ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዕድገትን ለማረጋገጥ ብሔራዊ መግባባትን መፍጠርና ይቅር መባባልን ተግባራዊ ማድረግ።

5. <u>ምህረት ስለመስጠት</u>

1/ ከግንቦት 30/2010 ዓ.ም በፊት የሚከተሉትን የወንጀል ድርጊቶች ፈጽሟል በሚል ተጠርጥሮ የሚፈለግ፣ በምርመራ ላይ ያለ፣ የወንጀል ክስ የተመሰረተበት ወይም የጥፋተኝነት ፍርድ ውሳኔ የተላለፈበት ሰው ወይም የሽብርተኛ ድርጅት ምህረት ተደርጎለታል፤

ሀ) በሕገ መንግስትና በሕገ መንግስት ሥርዓት ላይ የሚደረግ ወንጀል (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 238)፤

www.ethiopianlawgroup.com

ማለት መደበኛ ወይም ወታደራዊ ፍርድ ቤት ነው፤4/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ወይም የሕግ ሰውነት ያለው ሰው ነው፤

5/ በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተመለከቱ የወንጀል ድርጊቶችን ፈጽሟል ተብሎ ተጠርጥሮ በሚፈለግ፣ በምርመራ ላይ ያለ፣ የወንጀል ክስ የተመሰረተበት ወይም የጥፋተኝነት ፍርድ ውሳኔ የተላለፈበት ሰው ወይም የሽብርተኛ ድርጅት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

4. <u>ዓላማ</u>

ይህ አዋጅ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

1/ በተለያዩ የወንጀል ድርጊቶች የተሳተፉ ሰዎች ለድርጊታቸው የወንጀል ተጠያቂነታቸውን በጠቅላላው በመሰረዝ ወደ ሕብረተሰቡ ተቀላቅለው በሀገር ግንባታ ውስጥ የበኩላቸውን ድረሻ እንዲያበረክቱ ማድረግ፣

2/ የፖለቲካ መብታቸውን ተግባራዊ ለማድረግ በመንቀሳቀሳቸው ምክንያት የወንጀል ተጠያቂነት ሊያስከትል ይችላል በሚል ስጋት በተለያዩ የዓለም ሀገራት የሚገኙ ኢትዮጲያዊያንና ትውልደ ኢትዮጲያዊያን ምህረት በመስጠት ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤

3/ ጥላቻና የእርስ በእርስ ጥርጣሬን በማስወገድ በመፈቃቀድና በአንድነት የተጀመረውን የሀገራችን ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዕድገትን ለማረጋገጥ ብሔራዊ መግባባትን መፍጠርና ይቅር መባባልን ተግባራዊ ማድረግ፡፡

5. <u>ምህረት ስለመስጠት</u>

1/ ከግንቦት 30/2010 ዓ.ም በፊት የሚከተሉትን የወንጀል ድርጊቶች ፈጽሟል በሚል ተጠርጥሮ የሚፈለግ፣ በምርመራ ላይ ያለ፣ የወንጀል ክስ የተመሰረተበት ወይም የጥፋተኝነት ፍርድ ውሳኔ የተላለፈበት ሰው ወይም የሽብርተኛ ድርጅት ምህረት ተደርጎለታል፤

ሀ) በሕገ መንግስትና በሕገ መንግስት ሥርዓት ላይ የሚደረግ ወንጀል (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 238)፤

www.ethiopianlawgroup.com

6. **ስለተወረሰ ንብረት**

በዚህ አዋጅ መሠረት ምህረት የተደረገለት ማንኛውም ሰው ንብረቱ እንዲወረስ በፍርድ ቤት ተወስኖ ከሆነ ምህረት ስለተደረገለት የተወረሰው ንብረት እንዲመለስለት የመጠየቅ መብት አይኖረውም፡፡

7. **ምሕረት ስለተደረገለት ሰው**

ማንኛውም ምህረት የተደረገለት ሰው፡-

1/ ከማሕበረሰቡ ጋር ተቀላቅሎ ሰላማዊ ህይወት የመምራት መብት አለው፤

2/ ምህረት በተደረገለት ወንጀል ምክንያት በግል ጥቃት ለማድረስ የሚፈልግ ሰው ካለ በአካባቢው ባህልና ልማድ መሠረት መታረቅ ይኖርበታል፤

3/ በማናቸውም የሕግ አስፈፃሚ አካል ክትትል እየተደረገበት ከሆነ ክትትሉ እንዲቆም፣ በምርመራ ሒደት ላይ ከሆነ ምርመራው እንዲቋረጥ፣ በክስ ሒደት ላይ ያለ ከሆነ ክሱ እንዲቋረጥ ወይም በማረሚያ ቤት ቅጣት መፈፀም ላይ ከሆነ እንዲለቀቅ ይደረጋል፡፡

4/ ወደ ሀገር መግባቱን፣ ወደ ማህበረሰቡ መቀላቀሉን ፣ሰላማዊ ኑሮ ለመምራት መወሰኑን እና በአጠቃላይ የምህረቱ ተጠቃሚ መሆኑን ለፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ወይም ለክልል ፍትህ ቢሮዎች በአካል በመቅረብ፣ በተወካዩ አማካኝነት፣ በስልክ፣ በፖስታ፣ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ወይም በማናቸውም ሪፖርት የማድረጊያ ዘዴ ይህ አዋጅ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከፀደቀበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት ስድስት ወራት ውስጥ ሪፖርት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

5/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 4 መሰረት በስድስት ወራት ውስጥ ሪፖርት ያላደረገ ሰው መንግስት በልዩ ሁኔታ ካልወሰነ በስተቀር የምህረቱ ተጠቃሚ አይሆንም፡፡

8. **አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሀምሌ 13 ቀን 2010 ዓ.ም.

ሙላቱ ተሾመ (ዶ/ር)

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ

ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት